## 1. የጦርነት ወይም የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ፍጻሜና የፖለቲካ ሽግግር ጥያቄ

### 1.1. ከፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ወደ ዲሞክራሲ ሽግግር

በአቶ ዥንሳ ነስ:- ዓለም አቀፍ የታሪክ ምርምር ማዕከል
ባርሴሎና — ስፔን

ስፔን ከፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለመውጣት የቻለችው ከረዥም ጊዜ የታሪክ ሂደት በኋላ ነው:: በዚች አገር መጀመሪያ የሶስት ዓመት የርስ በርስ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ ለ36 ዓመታት የጄነራል ፍራንኮ ዲክታቶሪያል አገዛዝ ተከተለ:: ወደ ዲሞክራሲ የሽግግር ሂደት ለመጀመር የጄነራሉን ሞት ለመጠበቅ ተገደደናል::

ይህም ሆኖ ጄነራሉ ባረፉበት ጊዜ ከአርባ ዓመታት ቀደም ሲል የእርስ በርስ ጦርነትን የቀሰቀሱት መነሻ ምክንያቶች አሁንም እንዳሉ ነበሩ:: በ1933 ዓ.ም. የእስፔን ሪፐብሊክ መመስረት የሕዝቡን ገጣሽ ያስቆጣ ከስተት ነበር:: የሀገሪቱን የፋይናንስና ኢኮኖሚ የሚቆጣጠሩ ኃይሎች የካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣ ሠራዊቱ...እነዚህ ሁሉ የሪፐብሊኩ ተቃዋሚዎች ነበሩ::

በዚህ ላይ ደግሞ ሃገሪቱ የብሄረሰቦች/ብሄሮች ችግሮች ነበሩት:: ሪፐብሊኩ ሲቋቋም ለአንዳንዶቹ ሪጂናል ኦቶኖሚ ታወቀላቸው:: ይህ ውሳኔ በሠራዊቱ ምንም ተቀባይነት አላገኘም ነበር:: ስለሆነም ሠራዊቱ አመጸ::ከዚህም አመጽ ሠራዊቱ በጦርነት አሸንፎ ወጣ:: ነገር ግን ሰላም አልተገኘም:: የጄነራሉ አገዛዝ በቆየባቸው 36 ዓመታት የርስ በርስ ጦርነቱ ምንጭ የነበሩት ምክንያቶች አንዳቸውም መፍትሄ ሳያገኙ ቀሩ::

በጦርነቱ ጊዜ 25 ሺህ ተቃዋሚዎች ተረሽነዋል:: 500ሺህ የሚሆኑ ደግሞ ወደ ፈረንሳይና ወደ ላቲን አሜሪካ ተሰደዋል:: በዚህ የተነሳ ስፔን ምሁራኗንና መሪዎቿን አጣች::

ግን ደግሞ ይህም ሆኖ የስፔይን ህብረተሰብ 36 ዓመታት ሙሉ ባለበት አልቆመም ነበር:: ለልማትና ለእርምጃ አመቺ በሆነው በአውሮጳ አህጉር ውስጥ ስለሆነች ብዙ ለውጦች ተካሂደዋል:: እንዲያውም አገዛዙ የተደራጀ ተቃውሞንም ሆነ የወዛደር የሙያ ንቅናቄ አፍኖ የያዘ ስለነበር ካፒታል ላላቸው አሰሪዎች ስፔን በጣም አመቺ አገር ነበረች ማለት ይቻላል::

በሌላ በኩል ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ ያላገኘው የብሄሮች ጥያቄም እየተባባሰ ሄደ ግን የብሄሮች ተቃውሞ አንዱ አካባቢው የተለያየ ነበር:: የባስክ አገር የትጥቅ ትግል ሲካሄድ ካታሎንያ ደግሞ የተካሄደው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ባህልን የማጠበቅና የማንከባከብ እንቅስቃሴ ነበር::

ሌሎች የተቃውሞ ንቅናቄዎችም እንደዚሁ በየጊዜው እየተነሱ በየጊዜው እየተመቱ ይጠፉ ነበር:: በፖለቲካ መነሻ የተፈጸሙት የመጨረሻዎቹ 5 የሞት ቅጣቶች ከጄነራሉ ሞት አንድ ወር ቀደም ብለው ነው የተካሄዱት ::

የጄነራሉ እረፍት ለዲሞክራሲ በር ከፈተ:: ግን ደግሞ የሳቸው ሞት ብቻውን በቂ አልነበረም:: ሁላችንም በንሀን እንደዚህ ለረዥም ጊዜ የቆዩ ችግሮችን ለመፍታት ከነባር አስተሳሰቦቻችን ወጣ ብለን መመራመር ነበረብን::

የጄኔራሉ እረፍት ካለፈው አገዛዝ ጨርሶ መቁራረጥን አላስከተለም የቀድሞው መንግሥት የተከላቸው ተቋሞች በሙሉ እንዳሉ ነበሩ:: ንጉሡ በጄኔራል ፍራንኮ ጥላ ሥር ያደጉ ሰው ነበሩ:: ስለሆነም ተቃዋሚ ኃይሎች በጥርጣሬ ዓይን ይመለከቷቸው ነበር:: በዚህ ላይ ደግሞ ሲናገሩና ሃሳባቸውን በይፋ ሲገልጡ ተሰምተው አያውቁም:: በተጨማሪም ለአና ለዴሞክራቶች በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ጥላ ሥር ያደገ ሰውና በዚሁ በፈላጭ ቆራጭ ገዥ አማካኝነት ለንጉሥነት የታጨ ሰው ለመቀበል በጣም አስቸገርን ነበር::

የተቃዋሚ ኃይሎችን ሁኔታ ብንወስድ በጣም የተለያዩ እንደነበሩ እናያለን:: ከኮሙኒስት አንስቶ እስከ ሊብራል ድረስ የተለያዩ ቀለማት ነበራቸው:: ብዙ ሰዎች ጄኔራል ፍራንኮ ሲሞቱ ስፔን ወይ እንደጣልያን አገር በክርስቲያን ዴሞክራቶች አገዛዝ ወይ ደግሞ በኮሚኒስቶች እጅ ትወድቃለች የሚል ግምት ነበራቸው:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ከሁሉም ይበልጥ የተደራጀ ኃይል ያላቸው ኮሚኒስቶች ነበሩና::

በዚህ ሁኔታ እንገዲህ ተቃዋሚ ኃይሎች ከሁለት አንድ መንገድ መምረጥ ነበረባቸው ወይ ካለፈው ሥርዓት ጋር ጨርሶ መቁረጥ ወይም ደግሞ ቀስ በቀስ ለውጦችን እያካሄዱ መራመድ ከብዙ ውይይትና ውጣ ውረዶች በኋላ የፖለቲካ ኃይሎች ቀስ በቀስ እንለውጠው በሚለው ጉዳና ለመስማማት ቻሉ::ሱዋሬዝ የተባሉት የፍራንኮ ዘመን ሚኒስትር ይኸንን የሪፍርም ሃሳብ ለውሳኔ ህዝብ /ሬፈራንደም/ አቀረቡት ጸደቀ:: የግራ ፖርቲዎች በሬፈራንደሙ የድጋፍም የተቃውሞም ድምጽ ላይሰጡ ወሰኑ:: ሬፈራንደሙ እንዲጸድቅ ያደረገው ይህ የግራ ኃይሎች ድምጽ ላለመስጠት ያደረጉት ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል::እኔ እራሴ በዚያን ጊዜ ፈረንሳይ አገር ነበርኩኝ:: ምንም እንኳን የሶሻሊስት ፖርቲ ታጋይ ብሆንም ለሀገሪቱ የሚያዋጣት ይህ የሪፍርም ጉዳና ነው ብዬ ሙሉ በሙሉ አምን ነበር::

ከዚህ በኋላም ፍራንኮ የዘረጉት አስተዳደር እንዳለ ቀጠለ:: ምንም እንኳን በጊዜው የነበረው ብሄራዊ ምክር ቤት በህዝብ የተመረጠ ሳይሆን በፍራንኮ የተሰየመ ቢሆንም ቀሉ አባላቱ ራሳቸው ምክር ቤቱ እንዲበተንና ሌላ ምርጫ እንዲካሄድ ወሰኑ:: በዚህ በአዲሱ ምርጫም የቀድሞው የፍራንኮ አገዛዝ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ተሳተፉ:: ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ስዋሬስ የፍራንኪስቶች ፖርቲ መሪ ሆነው ነበር ለምርጫ የቀረቡት:: እርግጥ እነዚህ ሰዎች በምርጫው መሳተፍቸው ለብዙ ዴሞክራቶችና የቀድሞ ተቃዋሚዎች የቀየ አምን እንደመከዳት ሀ ታይተአቸውና አስጠንቋቸው ነበር::

አዲሱ ሁኔታ የወዘደር ሙያ ማህበራት እንዲደራጁ አስቻላቸው:: ብዙ ማህበራት ሲቋቋሙ ሁለት ጎልተው የሚታዩ ነበሩ:: "የወዝ አደር ኮሚሽን" የሚባሉት በአንድ በኩል "የወዛደሮች አጠቃላይ ማህበር"የሚባለው ደግሞ በሌላ በኩል በቀድሞው አገዛዝ ሥር እንክ ብካቤ ይደረግላቸው የነበረት ሙያ ማህበራት ቀስ በቀስ ከሰሙ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአሰሪዎች ማህበር በአስቸኳይ ተቋቋመ:: በመንግሥት አሳሳቢነት ተገናኝተው የሠራተኞችና የአሠሪዎች ማህበራት ለሶስት ዓመት የሚጸና ስምምነት ተፈራረሙ::

ቤተክህነትን በሚመለከትም ሂደቱ ያው ነበር:: ከእርስ በርስ ጦርነቱ በፊት ሪፑብሊኩ ሲቋቋም ዓለማዊና ፖለቲካዊ ስልጣኑን ተገፋ ነበር:: የፍራንኮ አገዛዝ ይኸንን ስልጣን መለሰላት:: ዴሞክራሲ ሲሰፍን ደግሞ ይህን ስልጣን ተነጠቀች:: ግን በአርባ ዓመት ውስጥ ቤተክህነትም ራሷም ብዙ ለውጥ አድርጋ ስለነበር በተለይ ደግሞ ወጣት ቀሳውስት

ከቀድሞው ዓይነት አስተሳሰብ የተሳቀቀ ስለነበረ አዲሱ ሁኔታ ብዙም ችግር አለፈጠረም ነበር::

ከዓጼ ኮንስታንቲን ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክህነት ፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ላትገባና በህብረተሰቡ ውስጥ የሰላምና "የሽምግልና" ቦታ ብቻ ለመያዝ ተስማማች::

አሠሪያቸና ባለካፒታሎች መጀመሪያ ላይ ተጠራጣሪ ነበረ:: ፍራንኮ ከሞተ በኋላ ለአምስት ዓመታት ያህል ከሀገሪቱ ብዙ ካፒታል ወደ ስዊትዘርላንድ ባንኮች ያሸሹ ነበር:: ነገር ግን በሠራተኞቹና በአሠሪያቹ መሃከል የተፈረመው ውል እንዲረጋጉና ካፒታላቸውን ወደ ሃገር እንዲመልሱ ገፋፋቸው::

የቀረው እንግዲህ ሠራዊቱ ነበር:: ለ36 ዓመታት ያህል ከሥርዓቱ ብዙ ጥቅም ሲያገኝ የቆየ ክፍል ነው:: ነገር ግን ጦርነትን ያሸነፉት ወታደሮቹና መኮንኖቹ አሁን አርጅተዋል:: ወጣቶቹ ደግሞ ዲሞክራሲን ለመቀበል ዝግጁ ነበረ:: በዚህ በኩል የተፈጠረ ረው አስጊ ሁኔታ በባስክ አገር የሚካሄደው የሽብር ፈጠራ ዘመቻ ብቻ ነበር ማለት ይቻ ላል:: በተለይ ደግሞ ይህ ዘመቻ ያተኮረው ከፍተኛ መኮንኖችን መግደል ላይ ስለነበር በጦር ሠፈሮች አካባቢ ብዙ ማጉረምረም ነበር::

በዚህ ሁኔታ ነው 23 ፌብርዋሪ 1981 ዓ.ም. በዓለም የመጀመሪያው በቴሌቪዥን በቀጥታ የተላለፈ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የተካሄደው "ሲቪል ዘብ" የተባለው የሠራዊቱ ክፍል ፓርላሜንቱንና የመንግሥት ባለሥልጣኖቹ ስብሰባ ላይ እንዳሉ አፈናቸው:: ይህን ጊዜ ነው ንጉሡ በቴሌቪዥን ቀርበው ወታደሩን ወደ ጦር ሠፈሩ እንዲመለስ ትእዛዝ የሰጡት በርግጥ የዚያን እለት ነው በስፔን ዲሞክራሲ አሸነፈ ሊባል የሚቻለው፤በዚያን እለት ነው ንጉሡም በእርግጥ በህዝቡ ዘንድ ስመጥሩ ለመሆንና በዲሞክራቶቹም ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የበቁት::

እንግዲህ ከስፔን ለምድ ሁለት መሠረታዊ ትምህርቶች ማግኘት ይቻላል ብዬ እገምታለሁ፤

1/ ሽግግሩ መሳካት የቻለው ሁሉም ወገን አቋሙን በማሸጋሸግና ለመቻቻል ባደረገው ጥረት ሲሆን፤ የግራም ሆነ የቀኝ የፖለቲካ ኃይሎች አሠሪያቹም ሆኑ ሠራተኞቹ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ነው::

2/ ፍራንኮ ባረፈበት ጊዜ የስፔን ህብረተሰብ ከፖለቲካዊ ሥርዓት አለፍ የሄደና የተራመደ ህብረተሰብ ነበር:: ይህ ቅድመት በኢኮኖሚው መስክ በጣም ገለጸ ነበር:: በፈላጭ ቆራጭ አገዛዙ ሥርም ሆነን የገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ነበርን:: ግን ኢኮኖሚው ማደጉን እንዲቀጥል ሃገሪቱ ይበልጥ ከፈት ያለ ሁኔታና ብዙ ካፒታል ያስፈልጋት ነበር:: አሠሪያቹ የፍራንኮ አገዛዝ ኢኮኖሚውን ዝብትቦ በመቆጣጠር ያወጣቸው ህጐች አላሠራ እንዳላቸው ተገነዘቡ:: ለውጥ ይፈልጉ ነበር:: ይህ ቅድመት በማህበራዊ ጉዳዮቹም ቢሆን ጎልቶ ይታይ ነበር:: ለምሳሌ ያህል የፍራንኮ አገዛዝ በጣም ወግ አጥባቂ ሆኖ ስለቀጠለ አንዳንድ ፊልሞች "ክለገናን ያስፋፋሉ" እየተባሉ ሳንሱር አያልፉም ነበር:: ስለሆነም ህዝቡ ሥራ ፋ ብሎ ድንበር እያቋረጠ እነዚህን ፊልሞች ፈረንሣይ አገር እየመጣ ያይ ነበር::

## 2. በፖላንድ የኮሚኒስት አገዛዝ አወዳደቅ

### በአቶ በይሊን የታሪክ ተመራማሪና ጋዜጠኛ

ፖላንድን በሚመለከት ሂደቱን "የአንድ ርእዮተ ዓለም መሞት" ሂደት ብለን ልንሰይመው እንችላለን፡፡ በኮሚኒስቶች አገዛዝሥር በነበርንበት ዘመን የተቃዋሚ ኃይሎች ትግል ግልጽ የሆነ መድረክ ነበረው፡፡ ትግሉ እውነት በአንድ በኩል፤ ቅጥፈትና ጭቆና በሌላ በኩል የተፋጠጡበት ነበር፡፡ የህዝቡን ምኞትና ጉጉት የሚያንጸባርቁ ሁለት ተቋሞች ነበሩ፡፡ በአንድ በኩል የፖላንድ የብሄራዊ ማንነት ምልክት የሆነችው ቤተክህነት ነበረች፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን በደንብ ያልተደራጀና ያልተዋቀረ ቢሆንም ቀሉ ብሄራዊ፣ ማህበራዊ የገበሬዎችን ጥያቄዎች ይዞ የሚንቀሳቀስ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ነበር፡፡

ከርእዮተ ዓለም ትግል አንጻር ሲታይ "የድሮው ዘመን" በጣም ቀላል ነበር ሁላችንም ማንንና ምንን እንደምንቃወም እናውቅ ነበር፡፡ እንዴትም እንደምንታገል እናውቅ ነበር፡፡

ዛሬ ሁሉም ነገር እንዲህ ግልጽና ቀላል ነው ማለት አይቻልም፡፡ አዋሳኙ ወቅት በሶሊዳሪቲ ንቅናቄና በአገዛዙ መሃከል በጠረጴዛ ዙሪያ የተደረገው ድርድር ነበር፡፡ በዚህ ሳቢያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለአንዳች ደም መፋሰስ የኮሙኒስት አገዛዝ ተገረሰሰ፡፡ ግን ይህ እንዲሆን ለቀድሞው አገዛዝ አንዳንድ ዋስትናዎችን መስጠት ነበረብን፡፡ ይህንን በመስጠታችን አንዳንዶች የፖላንድ ሽግግር ውድቅ ነው እስከ ማለት ደርሰዋል፡፡ የኮሚኒዝም አወዳደቅ እንደዚህ በለሰለሰ ሁኔታ በመካሄዱ የተቃዋሚውን ወገን መሪዎች እንደ ከሃዲያን የቆጠሩም አይጠፉም፡፡

አሁን እንደምናየው ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር ሶስት ዓይነት ችግሮች አጋጥመውታል፡፡

የመጀመሪያው የህዝቡ ሳይኮሎጂ ችግር ነው፡፡ ዴሞክራሲን በጣም ናፍቆ የነበረው ህዝ ይህ ዴሞክራሲ ሲመጣ "ስፔክታኩላር"ሆና አለመታየቱን ሊቀበል አልቻለም፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ዴሞክራሲ ሰውን "ራስህን ቻል" "እወቅበት" ከማለት አልፍ ምንም ርእዮተ ዓለማዊም ሆነ ሌላ ዓላማ አይሰጥም፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ሥርዓት ምንም ትንሽ ቢሆን ሁሉም ደመወዝና የኑሮ ዋስትና ነበረው፡፡ ዴሞክራሲ የግድ ይሸንን ዋስትና ለግለሰቦች አይሰጥም፡፡ የኮሚኒዝም ሥርዓት ከመበረቅ አንስቶ እስከ አርሻ ምርት መውደቅ ድረስ ላሉት ክስተቶች ሁሉ ማብራሪያና ገለጻ ማድረግ የሚችል ሥርዓት ነበር፡፡ ዴሞክራሲ ግለሰቦች ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮችም ሆነ ውድቀቶች ምክንያቶች መደርደር አትችልም፡፡

ኮሚኒስቶች መግዛት የቻሉት ህብረተሰቡን በመከፋፈል ለአንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች በማድላትና ጥቅሞችን በማካፈል ነበር፡፡ የእነዚህ ክፍፍሎች ርዝራዦች ዛሬም አሉ፡፡ ሁሉም ቀደም ሲል አገኝቷቸው የነበረት ጥቅሞች እንዲነኩበት አይፈልግም፡፡ ሁሉም የራሱን ጥቅም እስካልነካ ድረስ ሪፎርም ይደግፋል፡፡ በሱ ጥቅም ሲመጣበት ደግሞ ይቃወማል፡፡ በዚህ ነው ለምሳሌ የሶሊዳሪቲ ንቅናቄ መሠረት የወዛደር መደብ ዛሬ ያለፈውን ሥርዓት የሚናፍቁ ፀረ ሪፎርም የሆኑ ኃይሎችን ወደ መደገፍ በማዘመም ላይ የሚገኘው፡፡

በዚህ ላይ እንግዲህ የመጥው ጊዜፍራቻና በመንግሥት ደረጃ የሚንከባከብ የጋራ ዓላማ መጥፋት የሚፈጥራቸው ችግሮች አሉ:: ዛሬ በአለንበት ዲሞክራሲ መንግሥት ህብረተሰባዊ የሆኑ የበላይ ዓላማዎችን /ቫሊውስ/ አያራምድም:: የሀገሪቱን የእለት በእለት ችግሮች መፍታት ላይ የሚያተኩር መንግሥት ነው::

ሁለተኛው ችግር ህብረተሰቡን በመጠናወት ላይ ያለው ሌሎችን የማግለል በሽታ ነው:: "የማህበራዊ መቻቻል ማሽቆልቆል" የምንለው ክስተት አለ:: ይህ ያለመቻቻል ሁኔታ በሁሉም መስክ ይታያል:: ፀረ አይሁድ ስሜቶች እያደጉ መሄዳቸው፣ አክራሪ ብሔራዊ ስሜት ማየሉ በግራና በቀኝ የፖለቲካ ኃይሎች መሃከል ጠብ እየከረረ መምጣት፣ ዛሬ አንድ ሰው ትንሽ የግራ አስተሳሰብ አለው ብሎ ከተወነጀለ ከተረገመው ኮሚኒዝም ተለይቶ የሚታይበት ሁኔታ እየጠፋ መምጣቱ::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቤተክህነትም ራሷ አንድ ችግር ነች:: ቀደም ሲል ከአገዛዙ አንጻር ብቸኛ የህዝብ ተወካይነት ሚና ነበራት:: ዛሬ ዲሞክራሲ ሲሰፍን ቤተ ክህነት ይሸንን ሞኖፖሊ አጣች:: ግን የቆየ ሚናዋን ደግሞ መልቀቅ ተቸግራለች:: ስለሆነም፣ የፖላንድ ብሄረተኛነት ስሜትን ለማንከባከብና ለማጠናከር ትሞክራለች:: ግን ደግሞ ህብረተሰቡ በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ህብረተሰብ ነው:: በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ አስተሳሰቦች፣ ንቅናቄዎች፣ ዓላማዎች ያፏጣሉ:: በዚህ ሁኔታ ቤተክህነት የፖላንድ ብሄርተኛነት ስሜት ለማስፋፋት የምታደርገው ሙከራ ወገናዊ እያደረጋት፣ ወደ አንዱ ህብረተሰብ ክፍል እያስጠጋ ከሌላው ደግሞ እያራቃት ሄደ:: በመሃል የቀደመውን "የሽምግልና"ና ታዋቂነት ሚናዋን እያጣች ነው::

ሶስተኛው ችግር የፖለቲካ ኃይሎችና የሙያ ማህበራት ድክመት ነው:: የሙያ ማህበራት የአባላትን ድጋፍ ሳለማጣት ሲሉ ወዛደሩን መምራት ሳይሆን በሱ መመራት ይዘዋል:: በያለበት ያለአንዳች ጥናት፣ ያለአንዳች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የሥራ ማቆም አድማዎች ያካሄዳሉ ከሙያ ማህበራት አመራር ውጭ::

በፖለቲካውም መስክ የሚታየው የሸው ነው:: የህዝቡ ችግሮች በፖለቲካው መድረክ ላይ አይንጸባረቁም:: ስለሆነም አብዛኛው ህዝብ ፖለቲካ ውስጥ ያለመግባት አዝማሚያ እያሳየ ነው:: ይሸ በህዝቡና በፖለቲከኞች መሃከል ያለው መራራቅ በግልጽ የሚታየው ህዝቡ በምርጫ ጊዜ እያሳየ በመጣው ግድየለሽነት ነው:: ያለፈው የሜዘጋጅ ቤት ምርጫ ጊዜ አንዳንድ ቦታዎች ሌላው ቀርቶ ለምርጫ የቀረቡት ተወዳዳሪዎች እንኳን ሄደው ድምጽ አልሰጡም::

በፖለቲካና በህዝቡ መሃከል ያለው መራራቅ ባለፈው የፖላንድ ፕሬዚዳንት ምርጫ ጊዜ ከናዳዊው ነጋዴ ቲምኒስኪ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ማዞበስኪ የበለጠ ድምጽ ሲያመጣ የታየ ክስተት ነው:: የቲምንስኪ ጥሩ ውጤት በሁለት ምክንያቶች ሊገለጽ ይቻላል::

1/ ቲምኒስኪ ከሁሉ በፊት የሚያንጸባርቀው የፖላንድ ህዝብ ከጨባጩ ሁኔታ ለመራቅ ያለውን ጉጉት ነው:: ማዞበስኪ ደግሞ ህዝቡ ይሸንን አስቸጋሪ የሆነ ጨባጭ ሁኔታ እንዲጋፈጥ ይጠረታል:: "መጥው ጊዜ አስቸጋሪ ይሆናል፣ መንግሥት ሁሉንም ችግሮች መፍታት አይችልም..ወዘተ" የማዞበስኪ ዲስኩር እንደዚህ ነበር:: እነዚህን ሃቆች ከመጋፈጥ ይልቅ ህዝቡ በቲምንስኪ ጨባጭነት የሌላቸው አሸብራቂ ተስፋዎች ደርቢ መመሸግን መረጠ::

2/ በህዝቡ ሳይኮሎጂ ፖለቲከኞችን የመጠራጠር የፖለቲከኞች ዓለም ለህዝብ ዝግ የሆነ “የጠላት ሠፈር” አርጉ የመመለከት ሁኔት አለ:: ቲሚንስኪ በማዞቭስኪ አንጻር ያደርግ የነበረው የጥላቻና የጥርጣሬ ዲስኩር ቀደም ሲል ተቃዋሚ ኃይሎች ራሳቸው በሶሲያሊስቱ ዘመን በኮሚኒስት አመራር ላይ ያደርጉት የነበረውን ዘመቻ የሚመስል ነበር::

### 3. በምሥራቅ አውሮጳ የተደረጉት ለውጦች ተመሳሳይነትና ልዩነት

በአቶ ቤርናርድ ዱሪያና፣ የአውሮጳ ዜጎች ምክር ቤት

በመጀመሪያ ሶስት ታላላቅ አካባቢያችን መለየት የሚያስፈልግ ይመስለናል::

1/ መአከላዊ አውሮጳና የባልቲክ አገሮች
2/ ምሥራቃዊ አውሮጳ
3/ የሶቪየት ህብረት የቀረው ክፍል

በነዚህ አካባቢያች የሽግግር ሂደቶች የተለያዩ ነበሩ:: አንዳንድ ተመሳሳይ ነጥቦች ይገኙባቸዋል::

ሽግግሩ ያለ አንዳች አመጽ ወይም በትንሽ አመጽ አማካኝነት የተካሄደ ሽግግር ነው በሩማንያ እንኳን ቢሆን ከፍተኛ የሆነ ዓመጽ ተካሄደ ማለት አይቻልም::በእንደዚህ ዓይነት ሰላማዊ ሁኔታ የተካሄዱ ሽግግሮች በታሪክ ብዙም አልታዩ::ግን ደግሞ የዓመጽ አለመኖር የራሱ ችግሮች ፈጥሯል:: አሸናፊና ተሸናፊ በግልጽ አልተለዩም:: እንዲያውም አንዳንድ አስደናቂ ሁኔታዎች አሉ:: የቀድሞ የፖለቲካ መሪያች ያጠራቀሙት ሃብት ስለነበራቸው ዛሬ የኢኮኖሚው ቁቴርና የግል ሃብት ኢኮኖሚ ተቀዳሚ ተጠቃሚያች ለመሆን በቅተዋል:: ይህ ሁኔታ ውዥንብርና ብዙ ማጉረምረም ፈጥሯል::

በሁሉም አገሮች በተለያየ የእድገት ደረጃም ቢሆኑ ተቃዋሚ ኃይሎች ነበሩ ግን ተቃውሞው አብዛኛውን ጊዜ የሞራል ተቃውሞ ነበር:: አዲሶቹ መሪያች ሃገርን ለማስተዳደር ብቁ ዝግጅ አልነበረም:: ኢኮኖሚውን ለማካሄድ ዝግጅ ስላልነበረ “ኤክስፐርቶች” ነን የሚሉ ከያሉበት በመጡ ሰዎች ተጥለቀለቀ በፖለቲካ አመራር ልምድ ስላልነበራቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ለሚፈለቁት አዳዲስ ችግሮችና ግጭቶች ምፍትሄ ማቅረብ ተሳናቸው::

ማህበራዊ ድርጅቶች ህልውናቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ችግር አለባቸው:: በአንዳንድ ሃገሮች “ሲቪል ሶሳይቲው” በጣም ደካማ ነው:: ሶሊዳሪቲ በፖላንድ፣ ሲቪል መድረክ በቼኮስሎቫኪያ፣.. የፖርቲ ቅንጢያች ሆኑ ግን ደግሞ ከጀርባቸው ፖርቲ የላቸውም:: ዲሞክራሲን መገንባት የሚሞከረው ከታች ሳይሆን ከላይ ነው:: እንደዚህም በመሆኑ በዲክታቶርሺፖች መውደቅ የተከሰተውን ክፍት ቦታ የሚሞላ ኃይል ጠፋ:: ለብሄረተኛነትና ለፖፑሊዝም ሜዳው አመቺ ሆነ:: በሶቪየት ጆርጂያ የሄደን እንደሆነ አመራሩ የሚያስተላልፈው መልክት በብሄርተኛነትና በዘርኝነት የተበከለ መልእክት ሆኖ እናገኘዋለን:: የዚህ ውዥንብር መነሻ ግልጽ ነው:: በድንገት የተገኘው ድል ህብረተሰቡን ጎልቶ የሚታይ ጠላት ነሳው:: አሸናፊም ተሸናፊም በመጥፋቱ ህዝቡ ጠላት መፈለግ ያዘ:: ለመጣው ችግር ሁሉ ጥፋተኛው “ያኛው” ነው የሚባልበት ሁኔታ መጣ:: “ያኛው” የሚባለውን ማፈላለግ ተያዘ:: በዚህ ሁኔት “ያኛው” ከቅርብ የሚገኝ ጎረቤት ቢሆን ደግሞ ነገሩን ያቀለዋል:: መወነጃጀልና መቦጫጨቅ ተከተለ::

## 4. ዲሞክራሲያዊ ሽግግር በቺሊ፣

በአቶ ሉዊ ሚያራ የቺሊ ሶሻሊስት ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

ቺሊ በላቲን አሜሪካ ከታዩት ወታደራዊ ዲክታተርሽፖች አንዷ ብትሆንም ከሀገሪቱ ታሪክ የመነጩ ልዩነቶች የታዩባት ሀገር ነች::

መጀመሪያ ነገር ቺሊ የቆየ ዲሞክራሲያዊ ባህል ያላት አገር ነች:: ከ1811 እስከ 1913 ዓ.ም. ድረስ የሀገሪቱ ፓርላማንት ያለማቋረጥ ሠርቷል:: ፕሬዘዳንቱ በየ6 ዓመቱ ይመረጥ ነበር:: ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲያች ነበሩ:: ማህበራዊ ድርጅቶች /የወዛደርና የገበሬ ሙያ ድርጅቶች፣ የወጣት ማህበራት/ በብዛት ነበሩ::

ቤተክህነትን የወሰድን እንደሆነ እርግጥ ጠንካራ ነች ግን ደግሞ ዘመናዊ አስተሳሰብ ነበራት:: ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ በገዛ መሬቷ ላይ የመሬት ይዞታ ማሻሻል ያደረገችው ከ30 ዓመታት በፊት ነበር::

በ1970 ዓ.ም. ሳልቫደር አሌንዴ በፕሬዘዳንትነት ተመረጡ የፊደል ካስትሮ የቅርብ ወዳጅና ማርክሲስት ነበሩ:: ቀደም ሲልም ሚኒስትርና 25 ዓመት ተመርጠው ያገለገሉበት የፓርላማው ሊቀመንበርም ነበሩ:: ወደ ሶሻሊዝም ለሚደረገው ሽግግር "የቺሊ ጎዳና" የሚል ሃሳብ ነበራቸው:: ይህም ከመሣሪያ አፈሙዝ ሳይሆን ከምርጫ ሳጥን የሚፈልቅ ሶሻሊዝም ነበር:: ይኸንንም ፕሉራሊስና ዲሞክራሲያዊ ወደ ሆነ ሶሻሊዝም የሚያመራ "ሁለተኛው አማራጭ ጎዳና" ብለው ሰየሙት

ሥልጣን እንደያዙ ዲሞክራሲያዊ አሠራርን እንዳከበሩ ሆኖ በሃገሪቱ መሠረታዊ የሆኑ ለውጦችን ለማምጣት ሞከሩ:: ነገር ግን በዚያን ጊዜ በቺሊ የነበረው የፖለቲካ ኃይሎች ሚዛን በጣም አደገኛ ነበር:: የቀኝ የመሃልና የግራ ኃይሎች ተመጣጣኝ ኃይል ነበራቸው የህዝቡ ድምጽ በነዚህ ሶስት ኃይሎች መሃከል እኩል የተከፈለ ነበር::

የሳልቫደር አሌንዴ መመረጥ ይኸን ሥርዓት አናጋው:: ከፍተኛ ተቃውሞን ቀሰቀሰ ይኸ ደግሞ የአሜሪካኖች ብቻ ሳይሆን የውስጥ ኃይሎችም ተቃውሞ ነበር:: በዚህ ምክንያት ነው 1973 ፒኖሼ መፈንቅለ መንግሥት ሲያደርጉ ከፍተኛ ተቃውሞ ያልነበረው:: የፒኖሼ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ከተቀሩት የላቲን አሜሪካ ወታደራዊ አገዛዞች አንጻር ሲታዩ ሶስት አዳዲስ ነገሮች ነበሩት::

1/ ሥልጣን በከፍተኛ ወታደሮች ሳይሆን በሳቸው እጅ ብቻ ተጠራቀመ፣
2/ የጦሩ የበላይ አዛዥ እንደሆኑ ቀጠሉ፣
3/ በ1980 ዓ.ም. በሳቸው ተዘጋጅቶ በጸደቀ ህገ መንግሥት አማካኝነት ወታደራዊው አገዛዝ ፖለቲካዊ ሽፋን አገኘ::

በፖለቲካው አንጻር የማያፈናፍን አመራር የመሠረቱትን ያህል በኢኮኖሚው አንጻር ደግሞ እጅግ ሩቅ የሆነ ሊበራል ፖሊሲ ነበራቸው::

በዚህ ሁኔታ ነው 1983 ዓ.ም. የኢኮኖሚ ቀውስ የደረሰው:: 1982 በጠቅላላው በላቲን አሜሪካ በተለይ ደግሞ በቺሊ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ዓመት ነበር:: የሀገሪቱ ብሄራዊ ምርት 15.8 % አሽቆለቆለ:: ይህ ቀውስ በሃገሪቱ ከፍተኛ የተቃውሞ እንቅስቃሴ አስከተለ:: በየወሩ 11ና ቀን/ማለትም ፒኖሼ የኩዴታ የተደረገበት ቀንን

በማስመለከት/ "ብሄራዊ ተቃውሞዎች" በሚባል ስም የታወቁት ህዝባዊ ሰልፎች ይደረጉ ጀመር:: የዚህ ንቅናቄ መዓበር 1973 ዓ.ም. ጀምሮ የነበረውን የፖለቲካ መታፈን ሁኔታ ቀየረው::

ፒኖሼ ይህንን ተቃውሞ ከሰበሩ በኋላ እሳቸው በወሰኑት ወቅት ምርጫ እንዲካሄድ ሀሳብ አቀረቡ:: ፍላጐታቸውም በዚህ ምርጫ አማካኝነት የህዝብ ቡራኬ ለማግኘት ነበር:: በ1986 ዓ.ም. የፖለቲካ ተቃዋሚ ኃይሎች ይህንን የውሳኔ ህዝብ ሃሳብ ለመቃወም አልቻሉም:: ስለሆነም ወዲያውኑ ህዝቡ ለምርጫ ሲጋበዝ አሉታዊ ድምጽ በመስጠት ተቃውሞውን እንዲያሰማ ጥሪ አደረጉ:: ይሸንን ጥረታቸውንም ለማስተባበር አንድ የጋራ ኮሚሽን አቋቋሙ:: በዚህ አማካኝነት 13 የቀኝ የመሃልና የግራ ፓርቲዎች የሚሳተፉበት "ዲሞክራሲያዊ ቀንጅት" ተቋቋመ:: በዚህ መልክ በተደረገው ጥረት ፒኖሼ በምርጫ ተሸነፉ:: ይህም ሆኖ ከዚህ ውድቀታቸው በኋላ አንድ አመት ያህል በሥልጣን ቆይተው ሌላ ምርጫ አዘጋጁ"ዲሞክራሲያዊ ቀንጅት" ራሱን አጠናክሮ 17 ፓርቲዎችን እስከ ማቀፍ ካደገ በኋላ ለመጭው ምርጫ አንድ የጋራ እጩ ለማቅረብ ቻለ::

11 ማርች 1990 በቺሊ ታሪክ አዋሳኝ ወቅት ነው:: ፓትሪዮስ አልዊን ተመረጡ ፈላጭ ቆራጩ ፒኖሼ በነጻ ዲሞክራሲያዊ በሆነ ዘዴ ለተመረጡት መሪ ሥልጣናቸውን አስረከቡ:: ግን ደግሞ በሥልጣን ላይ ባቆዩበት የመጨረሻው ዓመት በተከታታይ ህገ መንግሥታዊ ማሻሻሎችን በማድረግ ከመንግሥት ስልጣን የተወሰነ ክፍል ከሳቸው እጅ እንዳይወጣ አርገው ነበር::

ለምሳሌ ያህል 9 ሴናተሮች ሾሙ:: እንደዚህም በመሆኑ ምንም እንኳን ፕሬዘዳንት አልዊን ከሴኔቱ ውስጥ 56 % ድጋፍ ቢኖራቸውም ብዙ ህጐችን ለማስጸደቅ ከፒኖሼ ደጋፊዎች ጋር የግድ መደራደር ይኖርባቸዋል:: በዚሁ ዓይነት ሁኔታ ደግሞ ከፍተኛው የህገ መንግሥት ፍርድ ቤት 7 ዳኞች ሾሙ ለይስሙላ የጸጥታና የአፈና ተቋሞችን አፈረሱ:: ግን ደግሞ የነዚህ ተቋሞች ስርሸብ ወደጦሩ ስርሸብ እንዲዛወሩ አደረጉ:: ራሳቸውንም ለ8 ዓመታት የጦሩ የበላይ አዛዥ አርገው ሾሙ::

በዚህ መልክ ነው ሠራዊቱ ከሥልጣን በሥነ ሥርዓት ያፈገፈገው:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ወታደራዊው አገዛዝ ሥልጣን በለቀቀበት ጊዜ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ እስከዚህም አስከፊ ሁኔታ ላይ አልነበረም:: እንዲያውም ጥሩ ሁኔታ ላይ ነበር ማለት ይቻላል:: በፒኖሼ አገዛዝ የመጨረሻ ዓመታት ኢኮኖሚው በዓመት ከ7 እስከ 10% ያድግ ነበር:: ለዚህ ነው ፒኖሼ "በቺሊ የኢኮኖሚ ተዐምር አካሂጃለሁ" እያሉ ወደ ጦር ሠፈራቸው የተመለሱ::

እንግዲህ ይህ ሽግግር ሙሉ በሙሉ የተሳካ እንደሆነ በኔ ግምት 5 ችግሮችን መወጣት ይኖርበታል::

ሀ/ የሰው ልጅ መብት ጉዳይ:: በዚህ በኩል ካስከፊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በኋላ ሁለት ዓይነት ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል:: የመጀመሪያ የፖለቲካ እስረኞች ችግር አለ:: ሁለተኛ ስላለፈው ዘመን ሀቅን በሚገባ አጉልቶ ማሳየት፣ ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂዎችን መቅጣት ያስፈልጋል:: ግን ይሸ እንዳይሆን የሠራዊቱ አባላት ሁሉንም ነገር የሠራነው በትእዛዝ ነው የሚል መከራከሪያ አሳቸው::

ለ/ የማህበራዊ ኑሮ ማሽቆልቆል ጉዳይ:: ወዛደሩና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋሞች ለ16 ዓመታት ምንም አልተደረገላቸውም:: እነዚህን እንደገና ለማቋቋምና ለማዳበር ተለቅ ጥረት ያስፈልጋል:: ግን ደግሞ የሀገሪቱ በጀት ይኸንን "ዕዳ" መክፈል አይችልም::

ሐ/ የአመጽና የሽብር ፈጠራ ጉዳይ፡— የመንግሥት የሽብር ፈጣሪ ተቋሞች መፍረስ የእነዚህ ተቋሞች የቀድሞ አባላት ወደ ግለሰብ አመጽና ሽብር ፈጠራ ሊያመራቸው ይችላል::

መ/ በሲቪሎችና በወታደሮች መሃከል መግባባትን የመፍጠር ጉዳይ:— ሠራዊቱ የራሱን ስተናሚ እጠብቃለሁ ካለ በምን ዘዴ ነው ዲሞክራሲን ወለበ ወገንበትና መግባባትን ማዳበር የሚቻለው?

ሠ/ ተቋሞችን ሁሉ ዲሞክራሲያዊ የማድረግ ጉዳይ:— ከዚህ አንጻር ህገ መንግሥቱንና የፍርድ ቤቶችን አሠራር ዘዴ ማሻሻል ያስፈልጋል:: ግን በየጊዜው ከሠራዊቱ ጋር መደራደር ከተገደድን ይኸንን እንዴት ማከናወን ይቻላል?

5. <u>የአልጀሪያ ሁለት ሽግግሮች</u>

በአቶ አብደልቃድር ጀሉል፣ ሶስዩሎጂስት
አልጀሪያ

በአለፈት 30 ዓመታት አልጀሪያ ሁለት የሽግግር ዘመናት አጋጥመዋታል:: የመጀመሪያው ነጻ በወጣችበት ዓመት በ1962 የተካሄደ ሽግግር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቅርቡ በ1988 የተጀመረው የሽግግር ሂደት ነው:: እነዚህን ሁለት ሽግግሮች ጠለቅ አድርገን ስንገመግማቸው አንዳንዱ "ሃቅ" ብለን ተቀብለናቸው የነበሩትን እምነቶች ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት እንገደዳለን:: የሽግግሩ ሂደት ብዙ ቅራኔዎች ነበሩበት በዚህ ላይ ደግሞ የዚህ ሂደት ውጤት ሰዎች ከጠበቁት ጋር የሚጣጣም አልነበረም::

ብዙ ሰዎች አልጀሪያ ነጻ ስትወጣ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ፈንጠዝያና እልልታ የነበረ ይመስላቸዋል:: ይህ እውነት አይደለም:: ሃገሪቱ ነጻ እንደወጣች የሽግግሩ ሂደት በሁለት ምክንያቶች የተነሳ አስቸጋሪና ውስብስብ ሆና ተከሰተ::

መጀመሪያ ነገር የቅኝ አገዛዙ ዘመን ጥሏቸው የሄደውን ጠንቆች መጋፈጥና መወጣት ያስፈልግ ነበር::

ሁለተኛው ደግሞ አዲሱ የፖለቲካ ሥልጣን መደላደል የቻለው ለነጻነት በታገሉት ኃይሎች መሃከል ከፍተኛ የሆነ የሥልጣን ትግልና ሽኩቻ ከተካሄደ በኋላ ነበር:: በዚህ መልክ አሸናፊ ሆኖ የወጣው ኃይል በህዝቡ ዘንድ የአገኘው ተቀባይነት 20 ዓመትም አልሞላም::

እርግጥ ነው የአርበኝነቱ ትግል በቆየባቸው 8 ዓመታት /ማለትም ከ1954 እስከ 1962 ዓ.ም./ ምንም እንኳን የውስጥ ቅራኔዎች ቢኖሩም ታጋዮች እነዚህን አቻለዉ የጋራ ጠላትን መቋቋም ችለው ነበር:: ምንም እንኳን በጦር ሜዳ ብዙ ሽንፈት ቢደርስም /እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን የቬየትናም ተዋጊዎች ያገኙትን ዓይነት ሚሊታሪ ድል የአልጀሪያ ነጻ አውጭ ሠራዊት እንዳላገኘውና የአልጀሪያ ድል ይልቁን የፖለቲካ ድል መሆኑን ነው/

ምንም እንኳን ከሚሊዮን በላይ የሚሆን የአልጀሪያ ህዝብ በጦርነቱ ቢሰዋም ይህ አንድነት አልተናጋም ነበር::

ግን ጦርነቱ እንዳለቀ ይህ አንድነት ወዲያውኑ ተናጋ:: የሥልጣን ቦታ ባዶ ከመሆኑ የቀድሞ የትግል ጓዶች እርስ በእርስ መነታረክ ጀመሩ:: ስለሆነም ከዚህ ትርምስ የወጣው ሥልጣን ህጋዊነትም በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትም አልነበረውም::

የ1962 ዓ.ም. የመጀመሪያ ወራት ወሳኝ ወራት ነበሩ በጊዜያዊው የአልጀሪያ ሪፐብሊክ መንግሥትና በብሄራዊው ነጻ አውጭ ሠራዊት መሃከል የነበረው ልዩነት ይፋ ወጣ:: ሠራዊቱ ለመንግሥት አልታዘዝም አለ:: የሃገሪቱ መሪዎች በመሃከላቸው ያሉትን ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንደማይችሉ አሳዩ::

በጁን ወር 1962 ዓ.ም. ትሪፖሊ የተደረገው የአልጀሪያ ነጻ አውጭ ግንባር ጉባኤ ይህ ድክመት የተንጸባረቀበት ጉባኤ ነበር:: የአዲሱ መንግሥት ፕሮግራም እንኳን ውይይት ቁርጥ ሳይነበብ እንኳን በድምጽ ብልጫ ጸደቀ:: ይህም የሆነበት ምክንያት ተሳታፊዎች በሙሉ ያተኮሩትና ማተኮር የፈለጉት እንዲት ነጥብ ላይ ብቻ በመሆኑ ነበር:: ዋናው ጥያቄ ሥልጣንን ማን ይወስዳታል የሚለው ጥያቄ ነበር:: በትእግሥት ተወያይቶ አንድ ስምምነት ላይ ከመድረስ ይልቅ ወደ ትሪፖሊ አውሮፕላን ጣቢያ እሽቅድድም ሆነ:: ማነው መጀመሪያ አውሮፕላን ይዞ ወደ አልጀሪያ የሚከረው? ይሸ ነበር የተሳታፊው ሁሉ ጭንቀት ቤን ቤላ አልጀርስ ደረሱ አይት አህመድ ቲዚ ኡዙ፣ ቡንበሳ ደግሞ ትሌምሰን ደረሱ:: የምእራብ ጋዜጦች አልጀሪያም እንደ ኮንጎ መሆኗ ነው እያሉ ይጽፉ ጀመር:: በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ ጠረፍ ላይ የነበረው ጦር ሰራዊት ወሳኝ ሚና መጫወት የቻለው:: ከማርክ ተንቀሳቅሶ አልጀሪያ ግዛት ገባ:: አመጣጡ እንደ ነጻ አውጭ ሠራዊትነት ሳይሆን የሥልጣን መጨቦጨ መሣሪያ ሆኖ ነበር:: አገሪቱ ነጻ በወጣች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በቀጠና 4 ከነበረው የአርበኞች ጦር ጋር ከፍተኛ ውጊያ ተደረገ:: በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ሞቱ::

አልጀርስ ከተማ ውስጥ ህዝቡ ይህንን ሁኔታ አጥብቆ ተቃወመ:: "ሰባት ዓመታት ተዋጋን ይበቃል" የሚሉ መፈክሮችን ይዞ በመውጣት ሰላማዊ ሰልፎች አደረገ:: ጦርነት እየተፋፋመ ሲሄድ የህዝቡ ጭንቀት በተባራሪ ጥይት እንዳያልቅ ብቻ ነበር::

እንግዲህ ከዚህ ተነስተን በአልጀሪያ በዚህ መልክ የተቋቋመውን መንግሥት እንዴት እናየው? ምንም ቢሆን የነጻይቱ አልጀሪያ መንግሥት መቋቋም ተደጋፊነትና ተቀባይነት /ሌጂቲማሲ/ ነበረው:: ግን ደግሞ ከውስጥ ደም መፋሰስ አማካኝነት አሸንፎ ስልጣን የያዘው የፖለቲካ ኃይል ሌጂቲማሲ ነበረው ለማለት አስቸጋሪ ነው::

ይህ የሚያሳየው ምንድን ነው? አንድ ህዝብ ከሚሊዮን በላይ ዜጎች ሰለሰዋ ብቻ ዘላቂ ዲሞክራሲን እንደማይጎናጸፍ በግልጽ ያሳያል:: የተቃውሞ ትግል ወይም የአርበኝነት ትግል መኖሩ ብቻውን የዲሞክራሲ ዋስትና አይደለም:: በዚህ ትግል ውስጥ በሀቅ የተሳተፈችም አልጀሪያ ከድል በኋላ እንደዚህ ተሆናለች ብለው አልገመቱም ነበር::

ከዚህ በኋላ በህዝቡና አሸናፊ ሆኖ በመጣው የፖለቲካ ኃይል መሃከል ለ20 ዓመታት የቆየ አንድ ዓይነት መቻቻል ሰፈነ:: ይህ መቻቻል የተገነባው በሚከተሉት መሠረቶች ላይ ነበር:: መንግሥት ህብረተሰቡን "የመናገር መብት የለህም፤የመቃወም መብት የለህም፤ምክንያቱም

ነጻነትን ያገናጸፍኩህ እኔ ነኝ አሁንም ቢሆን በለጸገናንና ርምጃን የማመጣልህ እኔ ነኝ ይለዋል። መንግሥት ዲሞክራሲን ሳይሆን የሃገር ነጻነትንና ማህበራዊ እድገትን የሚያስገኝ ኃይል ሆኖ ቀረበ። በእርግጥም በማህበራዊ መስክ ብዙ መሻሻሎችና እድገቶች ታዩ። ትምህርት በተለይ ለሴቶች በጣም ተስፋፋ የህዝቡ ገቢ በአማካኝ በአምስት እጥፍ አደገ።

ይህ መሻሻል የተገኘው በጊዜው በነበረው የሰላም ኢኮኖሚ ሁኔታ በመጠቀም በመቻሉ ነው። ይህ የዓለም አቀፍ ሁኔታ ሲለወጥ፣ ማህበራዊ እድገት በተከታታይ የህዝብ ቁጣዎች መገንፈል የጀመረት ቲዚዝ፣ ኡዙ፣ ኦራን፣ ካሳባ፣ ኮንስታንትን..ወዘተ በነዚህ ሁሉ ከተማዎች የህዝብ ቁጣዎች ገነፈሉ ቀደም ሲል መቻቻሉ የተገነባበት "ሁሉም የዕለት ጉርሱን ያገኛል" የሚለው መሠረት ፈረሰ።ህዝቡ ሥራ፣ ቤት፣ የተሻለ ኑሮ ጠየቀ።መንግሥት ይህንን ማቅረብ አልቻለም።ከዚህ ይልቅ ለችግሩ መፍትሄ ዲሞክራሲና የኢኮኖሚ ሊበራሊዝምን ፈቀደ። በ1988 ዓ.ም. የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ብሄራዊ መማክርት ሸንጎው ፓርቲዎችን የሚፈቅድ ህግ እንዲያጸድቅ አደረገ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፓርቲዎች እንደ አሸን መፍላት ያዙ። ግን ሁሉም ውስጣዊ አሠራራቸው ያው እንደ ሥልጣን ላይ ያለው ድርጅት ነው። ለፓርቲ ፕሬዚዳንትነት የሚቀርበው አንድ እጩ ብቻ ሲሆን እሱ ከተመረጠ በኋላ አብረውት የሚሠሩትን የፖሊት ቢሮውን አባላት ይመርጣል።

## 6. የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አወጋገድና ዲሞክራሲያዊ ሽግግር በሃይቲ

ዥን ሁግ ሄንሪስ፣ የምእመናን መረዳጃ አገልግሎት
ሃይቲ

ባለፉት 180 ዓመታት ሃያ የሚሆኑ ህገ መንግሥታት ተራ በተራ ከሥራ ላይ ቢውሉም ሃይቲ ምንም የዲሞክራሲ ባህል የሌለባት ሃገር ነች። በዚህ ሁሉ ዘመን በሃገሪቱ የተፈራረቁት ፕሬዚዳንቶች ከአንዱ በቀር ሌሎች በሙሉ ወታደሮች ነበሩ። በ1957 ዓ.ም. ዱቫሊዬ በተጭበረበረ ምርጫ አማካኝነት ሥልጣን ለመጨበጥ ቻለዋል። ከዚያ ትንሽ ቆይተው በ1964 ዓ.ም. የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት አርገው ራሳቸውን ሾሙ። ቀስ ብለው ደግሞ በ1971 ዓ.ም. የሃገሪቱ ፕሬዚዳንትነት በውርስ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍበትን ሥርዓትና ደንብ አወጡ። በዚህ መለከ ልጃቸው ዥን ክሎ-ዱቫሊዬ ፕሬዚዳንትነትን ከአባታቸው ወርሰው፣ እሳቸውም በበኩላቸው የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ተብለው እስከ 1986 ዓ.ም. ድረስ ሀገሪቱን ገዙ።

በዚህ ዓመት የዥን ክሎድ ዱቫሊዬ አገዛዝ በህዝብ ተገረሰሰ። ከዚያ ወዲህ ባለው 5 ዓመት ውስጥ ሶስት ሚሊታሪና ሁለት ሲቪሎች ሃገሪቱን መርተዋል። ከዚሁ ጋር በተያየዘ በሃገሪቱ ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መደራጀትና መጠናከር ጀመሩ። ለመጀመሪያ ጊዜም የሃገሪቱ ገበሬዎች ከህዝቡ 85% የሚሆኑት በፖለቲካው መድረክ ላይ ብቅ አሉ።

በማርች 1987 ዓ.ም. አዲስ ህገ መንግሥት ጸደቀ። በዚህ ህገ መንግሥት መሠረት በተለያዩ የመንግሥት ዘርፎች ማለትም በሥራ አስጸጻሚው በህግ አውጭውና በዳኝነት ሰጭው ዘርፎች መካከል ግልጽ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል ተደረገ። ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆነ በነጻ የሚሠራ የምርጫ ኮሚሽን ተቋመ። የዚህ ኮሚሽን ዓላማ ትክክለኛ የሆነ፣ ምንም ማጭበርበርና ማድላት የሌለበት ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ ሲሆን ተንተን ማኩት የተባሉት

የቀድሞው መንግሥት አፋኝ ቡድን አባሎች ለ10 ዓመታት ለምርጫ ከመቅረብ እንዲታገዱ የተወሰነው ውሳኔ ከሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ነበር:: ሀገ መንግሥቱ ከ90%.በላይ ድጋፍ አገኝቶ እንዲጸድቅ ካስቻሉት አንቀጾች አንዱ ይህ በተንተን ማኩተቸ ላይ እገዳ የሚያደርገው አንቀጽ ነው ተብሎ ይገመታል::

ይህ ሁሉ ሆኖም በኖቨምበር 1987 የተከረው የጠቅላላ ምርጫ ከመሳካት ይልቅ በደም ባህር ተጥለቀለቀ:: ይህም የሆነበት ምክንያት ከምርጫው የግራ ኃይሎች በአሸናፊነት ይወጣሉ ብለው የፈሩት አሜሪካኖች ለተጠነሰሰው የዓመጽ ሴራ ተባባሪ በመሆናቸው ነበር::

በእርግጥ ነጻ ሊባል የሚችል ሌላ ምርጫ የተካሄደው በዲሴምበር 1990 ዓ.ም. ነው ማለት ይቻላል:: ምርጫው የተካሄደው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቁጥጥር ሥር ሲሆን አባ አሪስቲድ ከዚህ ምርጫ በአሸናፊነት ወጥተው የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ሆኑ::

ፕሬዚዳንቱ ፌብርዋር 1991ዓ.ም. የመሃላ ሥነ ሥርዓት ፈጸመው ሥራቸውን ከጀመሩ ወዲህ ዲሞክራሲ ሰፍኖ እየተጠናከረ ይሄዳል የሚል ተስፋ በሃገሪቱ አለ::አሁን ሥልጣን ላይ ያሉት ኃይሎች አማኝ ክርስቲያኖች ሲሆኑ የተባበራቸው መመሪያ"ቴዎሎጂ ኦፍ ሊበሬሽን" የተባለው የክርስትና ፍልስፍና ነው:: ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ዝርዝር የተገባር ፕሮግራም አለወጣም:: በዚህም ምክንያት የህዝቡ ማጉረምረም እያደገ ሲሄድ ይታያል::

7. <u>የዚምባብዌ ሽገገር፣</u>

ወይዘሪት ፋጢት ተድ፣ ዚምባብዌ ፕሮጀክት
ቡላዋዮ ዚምባብዌ

ዚምባብዌ በ1890 ዓ.ም. የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ከሆነችበት ወቅት ጀምሮ ደቡብ ሮዴሽያ በሚል መጠሪያ በጥቂት ነጮች የምትገዛ አገር ነበረች:: ነጻነቷን የተጎናጸፈችው በ1980 ሲሆን ዛሬ የህዝቧ ቁጥር 11 ሚሊዮን ነው ተብሎ ይገመታል:: ከዚህ ውስጥ 1% ነጮች ናቸው::

ከለንደን ጉባኤ በኋላ በ1980 ዓ.ም. በተካሄደው ምርጫ የሮበርት ሙጋቤ"ዚምባብዌ አፍሪካዊ ብሔራዊ ህብረት" የተባለው ድርጅት አሸነፈ:: ከምርጫው በኋላ በነጮች ሰፈር ሽብር ነበር ማለት ይቻላል:: ይህን ሁኔታ በመመልከት ሮበርት ሙጋቤ ሥልጣን እንደያዙ ታሪካዊ ንግገር አደረጉ:: በዚህ ንግራቸው፣

"ዛሬ ሁላችንም እንደገና የአንድ አገር ሰዎች ሆነን የምንወለድበት ቀን ነው ከእንግዲህ ባለፈው የታሰርን ሰዎች ሳንሆን ወደፊት የምንመለከት ሰዎች ነን:: ሁላችንም አዲስ አመለካከትና አዲስ ፍቅር ይኑረን:: ትላንት ጠላቶች ነበርን:: ዛሬ የሃገራችን የጋራ ጥቅም ሁላችንንም ሊያስተሳስረን ይገባል::ሁላችንም እኩል መብት ሊኖረን ይገባል:: ትላንት ተጠላኝ ነበር ዛሬ ግን ለአዲሱ ሰላምና ፍቅር እንቅፋት ለትሆን አትችልም::" ከዚህ ንግገር በኋላ ጊዜ መጠቅለል ጀምረው የነበሩት ነጮች እንደገና መረጋጋትና መደላደል ጀመሩ:: የብሔራዊ ዕርቅ ፖሊሲ ወጣ ሮበርት ሙጋቤ መንግሥታቸውን ሲመሠርቱ ከራሳቸው ፖርቲ ብቻ ሳይሆን ከነጮ ማህበረሰብም መሃል ሚኒስትሮች ሰየሙ::

ይህም ሆኖ አንድ መቶ ሺህ የሚሆኑ ነጮች አገሪቱን እየለቀቁ ወጡ:: በዚህም ምክንያት በሃገሪቱ አስተዳደር ብዙ ቦታዎች ክፍት ሆኑ:: አንዳንዶቹ ወዲያውኑ ከውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ጨርሰው በተመለሱ አፍሪካውያን ዜጎች ተያዙ:: የሆና ሆኖ ግን የቀድሞው የአስተዳደር መዋቅር እንዳለ እንዲቀጥል ተደረገ::

በነጻነቱ ተጋድሎ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉት የገበሬዎች ጉዳይ ባስቸኳይ መፍትሔ ማግኘት ነበረበት:: ከገበሬው መሃል አንድ ሚሊዮን ያህል ወይ የተፈናቀሉ ወይ በእስር ላይ የሚገኙ የነበሩ:: አዲሱ መንግሥት ወዲያውኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወሰደ::

- በነጻነቱ ተጋድሎ የተሳተፉት ሶስት የታጠቁ ንቅናቄዎች ስለነበሩ የሶስቱ ድርጅቶች ሠራዊት ተዋህዶ አንድ ብሄራዊ ሠራዊት ተመሠረተ::
- ለአብዛኛው ህዝብ መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች /ውሃ፣መሬት፣ ትምህርት፣ የጤና አገልግሎት/ወዲያውኑ እንዲደርሰው ጥረት ተደረገ::
- በተለይ በነጮች የተያዘው የእርሻው ዘርፍ ለሀገሪቱ የምግብ ፍጆታ አማራጭ የሌለው ምንጭ ስለነበር እምነት ጠፍቶ ሥራው እንዳይጓደል የማስተማመኛ እርምጃዎች ተወሰዱ::
- ወደ ሀገር የሚመለሱ ስደተኞች መልሰው እንዲቋቋሙ የሚያስችሉ እርዳታዎች ተደረገላቸው::

የዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅት ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የእርሻ መሣሪያዎች በመስጠታቸው ይሽ ሁሉ በስነሥርዐቱ ለገበሬዎች እንዲከፋፈል ተደረገ:: የእርሻ ጥበብ አዋቂዎችም ለገበሬው ምክር እንዲሰጡ በያለበት ተደለደሉ:: በዚህ ላይ በመጀመሪያው የነጻነት ዓመት አስፈላጊው ዝናብ ጥሉ ስለነበር የዝምባብዌ የእርሻ ምርት እጅግ የሚያረካ ሆኖ ተገኘ::